ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

# ጥሪ ! ለሥርተከል አገራዊ ለወጥ

እስካሁን ከቱኒሲያ ተነስቶ ወደ ግብጽና ሌሎች አገሮች አሁን ደግሞ ወደ ሱዳን እየተዛመተ የመጣው የለወጥ እንቅስቃሴ የተጀመረውና እየተከናወነ ያለው በማንም ሳይሆን በሕዝብ ነው፡፡ በሕዝብ አነሳሽነት የሚደረግ የለወጥ እንቅስቃሴ በፖለቲካ ፓርቲዎች ጠባብ ፕሮግራም እስካልተጠለፈ ድረስ ወጤቱ ያሚ ብቻ ሳይሆን ዘላቂ ሰላምና ፍትሕ የማምጣት ዕድሉ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ የአገራችንን ሁኔታ በተመለከተ ለተለያዩ አካላት የሚከተሉትን የድርጊት ሃሳቦች ለማቅረብ እንወዳለን፡፡

### 1. ለኅብረብሔራዊና በኅሣ ለተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ለነጻአወጪ ግንባሮችና ንቅናቄዎች፡ –

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ይህ እንቅስቃሴ ሕዝባዊ እንደመሆኑ በሕዝብ ማሳሳትና መሪት ይጠበቅበታል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና ሕዝቡ የሚጠይቃቸውን በመሟላስ የሕዝቡ አገልጋይ መሆን ነው እንጂ የሕዝቡን እንቅስቃሴ ለራሳቸው የፖለቲካ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ማድረግ አይደለም፡ በመሆኑም ማንኛውም ድርጅት ትግሉን በመጥለፍና ለወጡን የራሱ ምርኮኛ በማድረግ ሕዝባዊ እንቅስቃሴውን የጥቃት ዒላማ ከማድረግ መቆጠብ አለበት፡፡ ይህ እንቅስቃሴ የሥልጣን ሽኩቻ የሚደረግበት ሳይሆን ሕዝባችን ነጻ የሚወጣበትና የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሠረት የሚጣልበት ሊሆን ይገባዋል፡፡

በብሔር የተደራጁ ድርጅቶችም ሆኑ የነጻ አወጪ ግንባሮችም ይህንን አጋጣሚ በማጠቀም አገሪቷን ለበታትን ከማቻል ድርጊት ፈጽሞ መቆጠበ ይገባቸዋል፡፡ ባለፉት ሥርዓቶች በርካታ የሕዝባችን ጥያቄዎች በሚፈለገው ሚለኩ አለመሟላሳቸው የሚታወቅ ነው፡፡ ስለሆነም የብሔር ተኮርና የነጻአወጪ ግንባሮች ጥያቄ ከዚህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ብቅ ብላ በምትወጣው አዲሲቷ ኢትዮጵያ ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ አብሮ የሚሟለስ መሆኑን ተገንዝባችሁ ሕዝባዊውን ለወጥ መቀላቀል ይጠበቅባችኋል፡፡

### 2. ለገዢው ፓርቲ አባላት፣ ካድሬዎች፣ ለመከላከያ፣ ለደኅንነት እና ለፖሊስ ሠራዊት፡ –

ህወሃት/ኢህአዴግ ባለፉት 20 ዓመታት ኢትዮጵያን በዘር ከፋፍሎ ለራሱ የሥልጣን ማራዘሚያ ሲያደርግ በተለይም የትግራይ ተወላጆችን እና ሌሎች ኢትዮጵያወያንን ሲጠቀም ቆይቷል፡፡ ሆኖም ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ቢያደርጉት የማይከፋፈልና <<ነብር ዥንጉርጉርነቱን እንደማይለቅ>> ፈጽሞ የማይለያይ ሕዝብ መሆኑን በተደጋጋሚ አስመስክሯል፡፡ በመሆኑም ገዢውን ፓርቲ እስካሁን በወገናዊነትም ይሁን በግል ጥቅም በማሳሳት ስትደግፉ የነበራችሁ፣ ማላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በመከራ እየኖረ እናንተ ለፓርቲው ባላችሁ ታማኝነት ብቻ <<በነጻነት>> ልትኖሩ አትችሉም፡ ምክንያቱም <<ሁሉም ነጻ ካልወጣ ማንም ነጻ መሆን አይችልምና>>፡፡ ስለሆነም ይህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እናንተንም ነጻ የሚያወጣ መሆኑን በማንዘብ ከሕዝብ ጋር የምትቆሙበትና ለትግሉ ድጋፍ የምትሰጡበት ሚልካም አጋጣሚ አሁን ነው፡፡ ዕርቅ ናፋቂውና ማዚሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎኑ እስከቆማችሁ ድረስ ለእናንተም ነጻነት እንደሚታገል አስተወላችሁ አጋርነታችሁን በምታገኙት አጋጣሚ ሁሉ እንድትገልጹ እናሳስባለን፡፡

ሕዝባዊው ለወጥ በቱኒሲያና በግብጽ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት ወቅት አገዛዞቹ የልዩ ጥበቃ ሠራዊታቸውን በሕዝቡ ላይ አዝምተው ነበር፡፡ ሆኖም ሠራዊቱና የልዩ ጥበቃ ኃይሉ የሰማው ለዓመታት ሲታዘዝ የነበረውን የሚሪዎቹን ቃል ሳይሆን የሕዝቡን ነበር፡፡ በሕወሃት/ኢህአዴግ ትዕዛዝ የሠራዊቱ አካላት እንዲሁም የደኅንነቱ ክፍል በሕዝባችን ላይ አሳዛኝ ድርጊት ሲፈጽም መቆየቱ የሚካድ ነው፡፡ አሁንም ተመሳሳይ ድርጊት የመከላከያና የፖሊስ እንዲሁም የልዩ ጥበቃው ኃይል እንዲፈጽም ከአቶ ማለስ ትዕዛዝ ሊሰጠው ይችላል፡፡ የተሰጣችሁን ትዕዛዝ የምትፈጽሙት የኢትዮጵያ አብራክ ክፍይ በሆኑት ወገኖቻችሁ ላይ መሆኑን በማወቅ ከዳግመኛ ስህተት እንድትቆጠቡ እናሳስባለን፡፡ <<ትዕዛዝ ነው የምፈጽመው>> በሚል ሰንካላ ምክንያት የኢትዮጵያን እናቶች ደግማችሁ እንዳታስለቅሱ፣ ይልቁንም ከወገናችሁ ጋር በማበር የሕዝባዊው ለወጥ አካል እንድትሆኑ በጥብቅ እናሳወቃለን፡፡

### 3. ለተማሪና ለወጣቶች

በኢትዮጵያ የለወጥ እንቅስቃሴ ወስጥ ተማሪዎችና ወጣቶች ከፍተኛውን ሚና እንዲሁም ማስዋዕትነት ሲከፍሉ ቆይተዋል፡፡ በአሁኑም የለወጥ እንቅስቃሴ ከፍተኛውን ሚና የምትጫወቱ እናንተ መሆናችሁ አይጠረጠርም፡ ስለዚህም ይህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሰላማዊና ሁከት አልባ ትግል እንዲሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ሕዝባዊ እንደመሆኑ የንግድ፣ የልማት፣ የትምህርትና የሃይማኖት ተቋማት አደጋ ላይ ከሚጥል ተግባር በመቆጠበ በ1997 የታየውን ዓይነት ሰላማዊ የተቃውሞ ትዕይንት የማሳየት ብቃታችሁን እንድትወጡ ጥሪ እናደርጋለን፡፡ የሚደረገው እንቅስቃሴ ከበቀልና ከጥላቻ ፍጹም የጸዳ እንዲሆንና ፍትሕን የምታገኙት ከመንገድ ላይ በኃይልና ሁከት ሳይሆን በአዲሲቷ ኢትዮጵያ በሚሠረቱት የፍትሕ ተቋማት መሆኑን ተገንዝባችሁ ራሳቸውን ከጥፋት ልትጠበቁ ይገባል፡፡ እንቅስቃሴው በቴክኖሎጂ የመገናኛ ወጤቶች ብቻ የሚታገዝ ሳይሆን አገር በቀል በሆኑ የተለያዩ መገናኛ ዘዴዎችንም በማጠቀም በተለያዩ ቦታዎች በአንድ ጊዜ ሊሆን ይገባዋል፡፡ የወጣቱና ተማሪው ኃይል የአጼ ኃይለሥላሴን ሥርዓት በገረሠሠበት ጊዜ ሕዝባችን አንዳሁኖቹ ፌስቡክና ትዊተር ይቅርና የስልክ አገልግሎት እንኳን በቅጡ እንዳልነበረው በማስብያሁኑ ትውልድ ብዙ የሚማረው አለ፡፡

### 4. ለነጋዴና ሠራተኛው ኅብረተሰብ

በቱኒሲያና ግብጽ የተከሰተው የዋጋ ግሽበት፣ የኑሮ ወድነትና ሥራአጥነት የለወጡን ሂደት እንዳቀጣጠለ በግልጽ የታየ ተግባር ነው፡፡ በኢትዮጵያም እየተከሰተ ያለው ከዚህ ፈጽሞ የተለየ አይደለም፡ እንዲያውም ነጋዴውን ኅብረተሰብ ከሕዝቡ ጋር ለማቃቃር ሆን ተብሎ በሸቀጦች ዋጋ ተመን ሰበብ እየተፈጸመ ያለው ተግባር ነጋዴውን ከኅብረተሰቡ ጋር ይበልጥ ሊያስተሳስረው የሚገባ እንደሆነ እናምናለን፡፡ ሠራተኛውም እንዲሁ በዚህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የዳር ተመልካች ሳይሆን ንቁ ተሳታፊ የመሆን ኃላፊነት

አለው፡፡ ጊዜው ከዕለት ጉርሱ በላይ የሚያስብበት ምቹ ወቅት መሆኑን በማንዘብ ነጋደው ከፍቅረንዋይ፤ ሠራተኛውም ከመንግሥት ምንዳ ባርነትነጻ በመውጣት የሕዝባዊእንቅስቃሴው ደጋፊአካልየምትሆኑበት ጊዜአሁን ብቻ ነው፡፡

## 5. ለሚዲያ እና በወጪ ላለው ኢትዮጵያዊ

በወጪ አገራት በሚዲያ ሥራ ሜለት በሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ የዜና ድረገጾች፣ ወዘተ ላይ የተሰማራችሁ በሙሉ የዚህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አካል በመሆን ድጋፍ ማስጠታችሁ የተሰማራችሁበት ሙያ የሚያስገድዳችሁ ነው፡፡ በመሆኑም ከወገናዊነት፣ ከጠብብነት፣ ከፋፋይነት፣ ወዘተ ፍጹም በጸዳ ሜለኩ ሕዝቡ ሊደርሰው የሚገባውን መልዕክት የማድረስ ኃላፊነት አለባችሁ፡፡ ዘመኑ ባፈራቸው የቴክኖሎጂ እሴቶችና ሌሎች ከዚህ በፊት ያልተፈተሹ ስልቶችን በመጠቀም ሚዲያዎች ወደኢትዮጵያ የሚደርሱብትን መንገድ መቀየስ ቀዳሚው ተግባራችሁ ነው፡፡ በወጪ ያሉ ወገኖቻችንም እስካሁን ለአንድ ፓርቲ ወይም ድርጅት እንደሰጣችሁት ዓይነት የገንዘብም ሆነ የሌላ ድጋፍ ሳይሆን እንቅስቃሴው ሕዝባዊ እንደመሆኑ ራሳችሁን ቀስቃሽ፣ አደራጅና ሜሪ በማድረግ የምታገኙትን ሚዲያ አገር ቤት ለሚገኙት ቤተሰቦቻችሁ፣ ጎረቤቶች፣ ዘመዶቻችሁ፣ ወዘተ እንዲደርሳቸው በማድረግ የትግሉ አጋር እንድትሆኑ እናሳስባለን፡፡ ሕወሃት/ኢህአዴግ በነፍስወከፍ ካድሬ በማዘጋጀት ሕዝቡን ሸብቦ እንደያዘ ሁሉም የሚያወቀው ሃቅ ነው፡፡ በመሆኑም በወጪ ያላችሁ ኢትዮጵያውያን እናንተም ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ምሥረታ ከሕዝባችሁ ጋር በማሰለፍ የዚህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አካል ልትሆኑ ይገባል፡፡ እንዲሁም ከኢትዮጵያ የምታገኙትን ዜና ለዓለምአቀፍ የመገናኛ አውታሮች – አልጃዚራ፣ ቢቢሲ፣ ሲኤንኤን፣ ወዘተ በማስተላለፍ የሕዝባችን ትግል ለዓለም እንዲደርስ የማድረግ ኃላፊነት የእናንተ ነው፡፡

## 6. ለምሁራን

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ደሃ አገራት ወስጥ ምሁራን ከፍተኛ ተደማጭነት አላቸው፡፡ የሚናገሩት ቃልም ሆነ የሚሰጡት አስተያየት ብዙሃኑ በአንክሮ የሚከታተለው ነው፡፡ አገራችን ኢትዮጵያ በደሃ አቅሟ ያስተማረቻቸው ምሁራን ጥቂት አይደሉም፡፡ በዚህም ምክንያት የለውጥ እንቅስቃሴ በሚካሄድበት አጋጣሚ ሁሉ የምሁራን ሚና ከፍተኛ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያ ወስጥም ይሁን በወጪ ያላችሁ ኢትዮጵያዊ ምሁራን የዚህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ አካል መሆናችሁ ለሕዝባችሁ ከምታበረክቱት ሜልካም ነገሮች በዋንኛነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ሕዝባዊው እንቅስቃሴ ወጤታማ እንዲሆን አቅጣጫ ጠቋሚ የሆኑ ሃሳቦችን በድፍረት በማፍለቅ ለትግሉ ወጤታማነትና ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ምሥረታየበኩላችሁን አስተዋጽዖ የምታደርጉበት ታሪካዊ አጋጣሚአሁን ነው፡፡

በሜጨረሻም – ይህ በ‹‹ግፋ በለው›› እና በ‹‹ተነስ›› ትዕዛዝ የሚጀምር ትግል ሳይሆን ጀማሪውም ሜሪውም ሕዝብ መሆኑን እንዲሁም ነጻነታችን ከፈጣሪ የተሠጠን እንጂ ከምዕራባውያን የሜቸረን አለመሆኑን ንቅናቄያችን በጽኑ ያምናል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ነጥቦች ላይ በተከታታይ መግለጫዎችን የምናወጣ ሲሆን ይህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና ፍትሕ እንደሚያስገኝ ንቅናቄያችን ያለውን ሙሉ ዕምነት ይገልጻል፡፡ ይህ እንቅስቃሴ የሕዝባችን የነጻነት ጥያቄ የሚሜለስበት፣ ለዘመናት ባገራችን ለተንሰራፉ ችግሮች የመፍትሔ መሠረት የሚጥልበት፣ ሰላምና ብሔራዊ ዕርቅ የሚሰፍንበት፤ ‹‹ከዘረኝነት ይልቅ ለሰብዓዊነት ቅድሚያ የሚሰጥባት›› አዲሲቷ ኢትዮጵያ የምትገነባበት ይሆናል፡፡

ስለሆነም እንደ ነብዩ እንባቆም ‹‹አምላክ ሆይ ስንጮህ የማትሰማን እስከ መቼ ነው? ከሚጸምበን ግፍ የማታድነን እስከ መቼ ነው?›› በማለት በየእምነታችን ‹‹የኢትዮጵያን እጆች ወደ ፈጣሪ እንዘርጋ››፡፡

ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ
*************************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ ሚዲያ ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም በስልክ (202) 725 -1616 በመደወል ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለሚዳት ይችላሉ፡፡*

